አዋጅ ቁጥር **137/1998** ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የተሻሻለው የስራ አመራር ኢንስቲትዩት

እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግ

ባራትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በብሔራዊ ክልሉ ወስጥ ጐልቶ የሚታየውን

የሰለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት ደረጃ በደረጃ

መቅረፍ ዘላቂ ለማትን ለመረጋገጥና ደህንነትን

ለማስወገድ የሚያበረክተው አስተዋጾ ከፍተኛ

እንደሚሆን በመታመኑ፤

በየደረጃው ተሰማርቶ የሚያገለግል ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት የሚቻልበትን መንገድ ለመፍጠር በስራ ላይ ለሚገኘው የሰው ኃይል የአጭርና መካከለኛ ጊዜ ስልጠናዎችን በስጠትና፣ የጥናት፣ የምርምር የምክር አገልግሎቶችን ለሕብረተሰቡ በማበርከት አጥጋቢ ውጤት የሚመዘገብበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤ በየእርከኑ የሥራ ሃላፊነት ተሰጥቷቸው ለሚቀሳቀሱት የልማት ሃይሎች በሥራ አመራር ጉዳዩች ላይ አተኩረው የሚሰጡትን ሥልጠናዎችና በዘርፉ የሚካሄዱትን የጥናት ምርምርና የምክር አገልግሎት አቅርቦት ሥራዎችን በተደራጀና ቀጣይነት ባለው መንገድ የማስተባበርና የመምራት አቅም ያለው መንግስታዊ አካል እንደገና በሕግ ማቋቋም፣ ማደራጀትና ስልጠና ተግባራቱን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው

ህገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ሥር

Proclamation No.137/2006

The revised proclamation issued to re-establish organize, and determine power and duties of the Management Institute of the Amhara National Regional State

WHEREAS, it is believed to ensure sustainable development and abolish poverty by alleviating the shortage of trained manpower, prevailing in the National Region; step by step, has high contribution

WHEREAS, it is found appropriate to produce efficient manpower that serves at every level by providing short and medium on-the job trainings and to create favorable condition by conducting study, research and counseling services to the society there of;

At WHEREAS it is found necessary to re-establish, organize and determine the power and duties or government body that gives trainings on different

በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የስራ አመራር ኢንስቲትዩት እንደገና ማቋቋምያ፣ ማደራጀትና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 137/1998 ዓ.ም>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. <<የልማት ሃይሎች ማለት በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ የስቪል ስርቪስና የመንግስታዊ የልማት ድርጅቶች አመራሮችና ሠራተኞች ሲሆኑ የስቪል ማህበራዊና የብዙሃን ማህበራት አባሎችን ይጨምራል።
2. <<የአጭር ጊዜ ስልጠና>> ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ከሶስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ የሚሰጥ ስልጠና ነው።
3. <<የመካከለኛ ጊዜ ስልጠና>> ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ከሶስት ወር ላመያንስና ከዘጠኝ ወር ለማይበልጥ ጊዜ የሚበልጥ ስልጠና ነው፤
4. <<የምርምርና የምክር አገልግሎት>ማለት ስራ አመራር ነክ በሆኑ ጉዳዩች ጥናትና ምርምሮችን የሚካሄድ፣ የመፍትሔ ሀሳቦችን የማመንጨትና የማማከር አገልግሎችን ይጨምራል።
5. <<ቢሮ>> ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አቅም ግንባታ ቢሮ ነው።(በአዋጅ ቁጥር 177/2003 ተሸሯል)

ክፍል ሁለት

ስለ ኢንስቲትዩቱ እንደገና ለማቋቋም፣ መደራጀት አላማ

fields and undertakes study, research and counseling supply works having a capacity to coordinate and direct the development forces who perform in the structure of the National Regional State bearing a responsibility;

Now, Therefore, the Council of the Amhara National Regional State pursuant to the power vested on it under sub-Article 3/1 of Article 49 of the constitution of the region, hereby issues this proclamation as follows.

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This proclamation may be cited as “The reestablishment, organization and determination of powers and duties of Management Institute, Proclamation No. 137/2006.”

2. Definition

Unless the context requires, otherwise, in this proclamation;

1. “Development Forces” means

ስልጣን

3. እንደገና ስለማቋቋም

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ስራ አመራር ኢንስቲትዩት/ ከዚህ በኋላ <<ኢንስቲትዩቱ>>እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰዉነት ያለው የክልሉ መንግስት አንድ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ አማካኝነት ተቋቁሟል።

2. የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል።(በአዋጅ ቁጥር 177/2003 ተሸሯል)

4. አላማ

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የልማት ሃይሎች በስራ አመራር ጉዳዮች በማሰልጠንና በዘርፉ የጥናትና ምርምር የምክር ሥራዎችን በማካሄድ ብቃት ያለረና በራሱ የሚተማመን አመራር መፍጠርና ለዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ የሚያበረክትበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

5. መደበኛ አድራሻ

የኢንስቲትዩቱ መደበኛ አድራሻ ባህር ዳር ከተማ ይሆናል እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ወስጥ በሌሎችአካባቢዎች የመስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊቋቁም ይችላል።

6. የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር

የኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት የኖሩታል፦

1. በየደረጃው የሚገኙ የክልላዊ መንግስቱ አካላት የሥራ አመራር ብቃት እንዲጉለብት አስፈላጊ የሆኑትን፣ የሥራ አመራር ስልጠናዎች፣ ምርምሮችና የምክር አገልግሎቶች ፍላጐት ያመጣል፣
2. በተጠና ፍላጐት ላይ ተመስርቶ ለክልሉ ልማት ኃይሎች ከሥራ አመራር ጋር የተያያዙ የአጭርና መካለለኛ ጊዜ

leaders and employees of civil service and governmental development organizations that are found at every level of the region, and includes members of civil society and civic associations.

2. “Short-Term training” means training to be rendered for a period not exceeding three months pursuant to this proclamation.
3. “Medium-Term Training” Means a training to be rendered for not less than three months and not exceeding nine months, pursuant to this proclamation.
4. “Research and Counseling Service” means carrying out studies and research on managerial affairs, initiating recommendations and includes counseling services.
5. “Bureau” means the Bureau of Capacity Building of Amhara National Regional State

PART TWO

Re-establishment, Organization, Objective and Power of the

ሥልጠናዎችን የሰጣል፣

3. የኢንስቲትዩቱ የሚሰው የሥልጠና፣ የምርምርና የምክር አገልግሎቶች ምን ያህል ጠጨባጭ ለውጥ ሊያመጡ እንደቻሉ እና እንደሚችሉ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት በየጊዜው ያሄዳል፤
4. በሀገሪቱ በተለይም በክልሉ የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት፣ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር በመደጋገፍና በመቀናጀት ይሠራል፤
5. የስልጣናና የጥናት ትሮጀክቶችን በመስጠት ከተለያዩ ምንጮች ገቢ የሚያገኝበትን ሁኔታ ይፈጣራል፤
6. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፤ዝርዝር አፈፃፀሙ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወሰን ሆኖ የስብሰባውን ገቢምለስልጠና፣ ለምርምርና ለምክር አገልግሎቶች ማስፋፊያ ይጠቀማል፤
7. የንብረት ባለቤት ይሆል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

7. ድርጅታዊ አቋም

የኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የሰራ አመራር ቦርድ
2. በክልሉ ርዕስ መስተዳደር የሚሰየሙ ዋናና ምክትል ዳሬክተሮች፣
3. ለስራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች

8. የቦርዱ አባላት

የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ቦርድ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታ፡-

1. የክልሉ አቅም ንግባታ ቢሮ ሃላፊ ----ሰብሳቢ

Institute

3. Re-establishment

1. The Amhara National Regional State Management Institute/ here in after referred

as the “Institute/” is hereby re-established by this proclamation as an autonomous Institution of the Regional State having its own juridical personality.

2. The accountability of the Institute shall be to the Bureau.

4.objective ,

The objective of the Institute is to create efficient and self confident management and facilitate conditions of contributing to sustainable development by training development forces of the region in management affairs and carrying out study and research works in the field to contribute for sustainable development.

5.

Regular Address

The regular address of the Institute

2.የክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ ኃላፊ/ ተወካይ/-----አባል

3.የክልሉ ሲ/ሰ/ኮሚሽነር/ተወካይ /--------አባል

4.የክልሉ ቴክኒክና ሙያትምህ ሥለጠና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሥራ አስኪያጅ/ተወካይ----አባል

5.ባህርዳር ዩኒቪርስቲ ፕሬዝዳንት/ተወካይ/----አባል

6. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር-----አባልና ፀሐፊ።

9.የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርድ በዚህ አዋጅ መሠረት ተተሪነቱ ለዕርሰ መስተዳደሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኢንስቲትዩቱ የአጭርና፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
2. ክልል አቀፍና ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን መሠረት በማድረግ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች አስመልክቶ በዋና ዳይሬክተሩ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን ረቂቅ የሥልጠና፣ የምርምርና የምክር አገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲዎችን መመሪያዎችንና የአሰራር ማንዋሎችን መርምሮ ያፀድቃል።
3. አሰልጣኞችና የተማራማሪዎችን የሙያ መሰላልና የደመወዝ መወሰኛ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ የፀድቃል።
4. የኢንስቲትዩቱ የአገልግለሎት ክፍያ መጠን ይወስናል፣
5. በክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ድጋፍ ዋና ዳይሬክተሩን መርጦ

shall be at Bahair Dar town; it may establish coordination offices in other areas of the region, as it deems necessary.

6. Power and Duties of the Institute

Pursuant to this proclamation, the Institute shall have the following power and duties:

l.to carry out studies on management training and the needs thereof, necessary to enhance management capacity of the bodies of the regional state at every level,

2.to prepare and conduct short and medium term trainings for development forces of the region based on assessed needs for training;

3.to carryout studies for the purpose of understanding the concrete change which is used from the training, research and counseling services and the capacity of same to do so,

4. to work in support and coordination with education,

በርዕስ መስተዳደሩ አማካኝነት ያሾማል፤

6. የኢንስቲትዩቱ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም የሂሳብ ሪፖርት ይገመግማል፣አቅጣጫዊችን ያስቀምጣል፤
7. የኢንስቲትዩቱ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዙንና ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
8. ዋና ዳይሬክተሩ የሚያቀርባቸውን ሌሎችሌሎች አጀንዳዎች መርምሮ ወሳኔ ይጣል፡፡

10. ስለቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ያደርጋል

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከቦርድ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተጉባኤ የሆናል፡፡
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በአብላጫ ድምፅ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንድሆነ ሰብሳቢው ያለበትን ወገን የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባ ስነሥርዓትና የውሳኔ አሰጣጥ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. የዋና ዳይሬክተር ሥልጣና ተግባር

1. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለርዕሰ መስተዳደሩ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ስር የኢንስቲትዩቱ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በዋና በሥራ ላይ ያውላል፡፡
1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ

training, study and research institutions • found in the country, particularly in the region,

5.to create conditions for the purpose of raising funds from various sources by preparing management trainings and, rendering counseling services.

6.to collect the appropriate fee from the concerned bodies for the service which it gives; and shall use the fee it collected for the expansion of training, [1] research and counseling services, the detailed execution to be determined by the Bureau of Finance and Economic Development;

7. To own property, enter into contract, and sue and be sued in its own name.

7. Organizational Structure

Pursuant to this proclamation, the Institute shall have the following bodies;

1. The management Board
2. The Director General and Deputy Director to be designated by Head of the Regional Government

ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉትን ዝርዝር ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

ሀ.የኢንስቲትዩቱ ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ያስተዳድራል፣ ይመራል፤

ለ. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ. የኢንስቲትዩቱ የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ሲፈቀድለትም በሠራ ላይ ያውላል፤

መ. ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጭ እንዲሆን ያደርጋል። በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

ሠ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ. ኢንስቲትዩቱን የሩብ ዓመት፣ ዓመታዊ የስራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱና ለቢሮው ያቀርባል፤

ሰ. ለቦርዱና ለቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ህጋዊያን ተግባራት ያከናውናል።

12. ስለምክትል ዳይሬክተሩ

ምክትል ዳይሬክተሩ በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾምና ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ፡-

1. ዋናው ዳይሬክተር በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና እርሱን ተክቶ ይሰራል፤
2. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናሉ።

ክፍል ሦስት

3. Employees necessary for the work.

8. The Board Members

The Management Board of the Institute shall have the following members:

1. The Regional Capacity Building Bureau head- Chairperson
2. The Regional Finance and Economic Development Bureau head/representative-Member
3. The Regional Civil Service Commission Commissioner /representative/ Member
4. the Regional Technical and Vocational Education and Training Promotion Agency Manager or representative- Member
5. The Bahir Dar University president/representative—Member
6. The General Director of the Institute member and secretary.

9. Power and Duties of the Board

Having been accountable to Head of the Government, Pursuant to this proclamation, the

Board shall have the following power

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. ስለ በጀት

የኢንስቲትዩቱን በጀት በክልሉ ምንግስት የሚመደብና ከሌሎች ምንዖች የሚገኝ ይሆናል።

14. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

1. ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይዛል።

2. ኢንስቲትዩቱ ሂሣብ መዛግብትና ግንዘብንም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራሉ።

15. የተሸሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸውን ሕጎች

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሸረዋል፡-

ሀ. የአማራ ብሔራዊ ክልል የሥራ አመራር ኢንስቲትዩቱን ለየወጣው አዋጅ ቀጥር 21.1989 ዓ.ም፤

ለ. የሥራ አመራር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 35/1991 ዓ.ም

ሐ. የሥራ አመራር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 95/1996 ዓ.ም።

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ መመሪያ ወይም የለተመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጠት በተሸፈኑት ገጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

16. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

በዚህ አዋጅ ውስጥ ለቦርዱ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው ለአዋጁ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

and duties:

1. examines and gives decision on the short, medium and long-term draft plan, annual work program and execution budget; follows the execution;

2. examines and approves the training, research and counseling service provision policies, [1] implementation strategies, directives and working manuals submitted to it by the General Director concerning the works of the Institute based on the regional and national polices and strategies.

3. examines and approves the career structure and salary determination directive of trainers and researchers submitted to it through the Director General

4. **decides on the amount of the service charge of the Institute.**
5. causes the appointment of the General Director by Head of the Government the upon support of the capacity Building Bureau.
6. evaluates the quarter and annual

17. አዋጁ ሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜታ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆል።

በባህርዳር

ሐምሌ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሮ(የአርትዖት ስህተት አይደለም)ዚዳንት

performance and financial report of the Institute and suggests direction.

7. ensures the force landing and usage of finance and property of the Institute.

8. examines and decides on other agendas to be submitted by the General Director.

10. The Meeting Time and Decision Provision Procedure.

1. The Board shall have regular meeting once a month; however, when it finds necessary, it may call urgent meeting at any time.
2. The presence of more than half of the Board members at meeting shall constitute the quorum.
3. The decisions of the Board shall be passed by simple majority vote, however, in case of a tie, the chairman shall have a casting vote.
4. Without prejudice to the provisions of this article, the Board may issue its own detailed meeting procedure and decision making

directive.

4. decides on the amount of the service charge of the Institute.
5. causes the appointment of the General Director by Head of the Government the upon support of the capacity Building Bureau.
6. evaluates the quarter and annual performance and financial report of the Institute and suggests direction.
7. ensures the force landing and usage of finance and property of the Institute.

8. examines and decides on other agendas to be submitted by the General Director.

10. The Meeting Time and Decision Provision Procedure.

1. The Board shall have regular meeting once a month; however, when it finds necessary, it may call urgent meeting at any time.

2. The presence of more than half of the Board members at meeting shall constitute the quorum.

3. The decisions of the Board shall

be passed by simple majority vote, however, in case of a tie, the chairman shall have a casting vote.

4. Without prejudice to the provisions of this article, the Board may issue its own detailed meeting procedure and decision making directive.

11.Power and Duties of the Director General

1. Having been accountable to the Board and Head of the Government, as the chief executive, the Director General of the Institute, implements the powers and duties stated under Art 6 of this proclamation.
2. Without prejudge to provision of sub-Art 1 of this Article, the General Director shall have the following powers and duties:

a) to direct, administrate and oversee the works of the Institute,

b) to employ, administer and dismiss the employees of the Institute in accordance with the Regional civil service law,

c) to prepare and submit the short, medium and long-term plan, annual performance program and budget draft and implements same upon approval;

d) to effect expenditure, in accordance with approved action plan and budget of the Institute and supervise the implementation of same;

e) to represent the Institute in the dealings' with the other third parties;

f) to prepare and submit quarterly, annual, performance and financial report of the Institute to the Board and Bureau,

g) perform such other legal activities assigned to it by the Board and Bureau;

12. Deputy Director

The Deputy Director is to be appointed by the Head of Government upon recommendation of the Director General and having been accountable to same;

1. to act on behalf of the General

Director in his absence or under the circumstances where he is unable to perform his normal duties;

2. to perform functions as may be given to him by the General Director,

Part Three

Miscellaneous provisions

13. Budget

The budget of the Institute shall be allocated by the Regional Government and other sources.

14. Books of Accounts

1. The Institute shall keep appropriate and complete books of account.
2. The books of accounts and financial as well as property documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or other external Auditors designated by the Board,

15. Repealed and inapplicable laws

1. The following are repealed by this proclamation

a) Proclamation No.21/1997, issued to establish the Amhara National

Regional Management Institute

b) Proclamation No.35/1998, issued to amend the proclamation provided for establishment of the Management Institute,

c) Proclamation No.95/ 2003, issued to re amend the proclamation provided for establishment of the Management Institute.

2.Any law, regulation, directive or customary practice, inconsistent with this proclamation shall be inapplicable on matters covered in this proclamation.

16. Powers to issue Directive

Without prejudice to the power of the Board vested to it by this proclamation, the Bureau may issue detailed directives necessary to full implementation of the proclamation.

17. Effective Date

This proclamation shall come into force since its publication date on the Regional State Zikere Hig Gazzette.

Done at Bahir Dar

	This 27th day of July, 2006 Ayalew Gobezie President of the Amhara National Region